# “ብርሌ ከነቃ ፥ ኣይሆንም እቃ”

**ይድረስ** ለህወሓት/ኢህኣዴግ ቱጃሮች፣ ኣባይ ጸሓየ፥ ስዩም መስፍን፥ ኣጃቢዎቹ ኣባዱላ ገመዳ፥ በረከት ስምኦን፥ ካሱ ኢላላና የገዢው መደብ ኣባላት!

ከኣረጋዊ በርሀ

“ብርሌ ከነቃ ፥ ኣይሆንም እቃ” የሚል የኣበው ኣባባል ኣርቆ ለሚያስብ ሰው በቂ መልእክት በሆነ ነበር፣ ታዲያ ለኣርቆ ኣሳቢነት ስላልታደላችህ እንደፈረደብኝ ዝርዝር ውስጥ መግባት ግድ ይሆንብኛል። መልእክቴ በሶስት ጉዳዮች ላይ የተካተተ ነው። 1ኛ/ የቀየሳችሁት የጨለማ መንገድ 2ኛ/ የፈጠራችሁት ኣጠቃላይ ቀውስ እና 3ኛ/ ከቀውሱ ኣዙሪት መውጫው የሚመለከቱ ናቸው።

በጥቅሉ ሲታይ የኣገዛዝ ገድፋችሁ የኢትዮጵያን ጥንታዊ፥ ማእከላዊና ዘመናዊ ታሪክ ያላገናዘበ፣ በማህበረ-ኢኮኖምያዊ ጥናት ያልተደገፈ፥ ስልጣንን በኣፈሙዝ መያዝ ብቻውን ዋናው ዓላማ ያደረገና የህዝብን ሓያልነት በጠብመንጃ ሊገዛ ያቀደ ደንባራ ትልም ነው ማለት ይቻላል። ይህ የጨለማ ዝላይ ሃገራችንን ዘመነ-መሳፍንትን ከሚያስንቅ ውስብስብ ቀውስ ውስጥ ከትዋት ይገኛል። በይበልጥ የሚያሳዝነው ደግሞ ይህ እዚህ ያደረሰንን ጨለምተኛ ጉዞ ኣሁንም ልትቀጥሉበት ማቀዳችሁና ለዚሁ ተብሎ የንጹሃን ደም በገፍ ማፍሰሳችሁ ነው። እዚህ ያደረሰን ዕቅዳችሁ ግድ ብሎ፥ ኣሁን እማያላውስ ሙት-ቦታ መድረሱና ከዚህ ኣጣብቂኝ በሰላም መላቀቅ የመላው ኢትዮጵያ ህዝብ የማይቀለበስ ወቅታዊ ጥያቄ መሆኑ ይታያችሁ ይሆን? ታያችሁም ኣልታያችሁ፥ የሰላሙን መንገድ ኣልቀበል ካላችሁ የኣመጽ ማዕበል ቀጣይ ነው።

ለነገሩ ብርሌው የነቃ ከጅምሩ ነው። ገና ስልጣን ላይ ሳትወጡ ጸረ-ኣንድነት የሆነውን የመገንጠል ኣባዜ ታራምዱ ነበር። የለም! የተነሳንበት ዓላማ ብሄረሰቦችዋን እኩል የምታስተናግድ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ስለሆነ መገንጠልን ወጊድ በሉ በማለት የተቃወምዋችሁን በሰበብ ኣስባቡ ስትገድሉ፣ ስታስሩ፣ ስታሳድዱና ያልሆነ ስም ስትቀቡ ኖራችሁ። የመገንጠሉ ደባ በሁሉም ዘርፎች ላይ ሲንጸባረቅ፥ በተለይ በባህር- በር ጥያቄ እና በስልጣን ክፍፍል ጉዳይ ላይ ጎልቶ በመታየቱ ሃገር-ኣቀፍ ተቃውሞ ኣስነሳ። ከጉዳይ ኣልቆጠራችሁትምና ከህዝቡ ጋር ሆድና ጀርባ፣ እሳትና ጭድ ሆናችሁ ዘለቃችሁ። ኢትዮጵያ የባህር በር መብትዋ ይከበር ብለው ድምጻቸውን ያሰሙ ሁሉ በጥይት ከመደብደብ ኣልፎ “ኢትዮጵያ ባህር በር ኣልነበራትም፣ ኣይገባትም” በማለት ተሳለቃችሁ / ኣፌዛችሁ። ሰላማዊ ተቃውሞ ባሰሙ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ስነ-ሞገታዊ መልስ መስጠት ስላቃታችሁ የጥይት ናዳ በመልቀቅ ብዙዎቹን ፈጃችሁ። ስልጣን ላይ ለመሰንበት ተቃዋሚን መግደል፥ ማጥፋት፥ ኣስሮ ማሰቃየት እንደ ዋና ኣሰራር ስለወሰዳችሁት ኣሁን ድረስ ትጠቀሙበት ኣላችሁ።  ይህ ሃገራዊ በደል ተከትሎ የሙስናው፣ የመጥፎ ኣስተዳደሩ፣ የመሬት ቅሚያው፣ የሓሳብ መግልጽና የእምነት ነጻነት ኣፈና፣ የስውር ግድያው በደሎች ኣነገሳችሁ።

በርግጥ መቃወም መብት እንደሆነ ቢገባችሁ ኖሮ እስካሁን ድረስ በተፈወሳችሁ ነበር፣ ካሁን ወድያ ይገባችሁ ይሆናል ብሎ መገመት ደግሞ ከየዋህነት ኣልፎ ቂልነት የሚያስብል ቢሆን ነው።  የመብት ጥያቄ የሚያነሳ ንቁ ዜጋ ሁሉ በጠላትነት፥ በኣሸባሪነት፥ በከሃዲነት ፈረጃችሁት። ገዢ ቦታ በጉልበት ስለተቆጣጠራችሁ መብት የናንተ ብቻ ሆነች። ኣምባገነንነት ይሉታል ይህ ነው።  ለሁሉም ገደብ ኣለውና፥ ስቃዩና መከራው የበዛበት ህዝብ ኣሁን ጥይት፣ ዱላ፥ እስር ቤት፣ መፈናቀልን ሳይፈራ በቃኝ ብሎ ተነሳባችሁ።

በዓለም ፊት ተጋለጡ ሲላችሁ፥ በ 100% ድጋፍ ሰጥቶን ምርጫ ኣሸነፍን ብላችሁ የዋሻችሁት መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው የተነሳባችሁ። በምርጫ ስርቆት ኣደባባይ ላይ ስትዋረዱ፥ ሓፍረተ-ቢስ ናችሁ እንጂ በሰለጠኑት ሃገሮች እንደሚደረገው፥ የውሸት ስልጣን በቃን ብላችሁ የሰረቃችሁት ስልጣን መልሳችሁ

ማስረከብ ነበረባችሁ፣ ኣልያም እምነተ-ድምጽ (vote of confidence) እንዲካሄድ ማድረግ ነበረባችሁ። ኣልሆነም፣ ኣይሆንምም። ለዚህ ዓይነቱ ዴሞክራሲያዊ ኣካሄድ ባእድ ሆናችሁ እንደቆያችሁት ባእድ ሁናችሁ ታልፋላችሁ። ለዚህም ነው "በጥልቀት እንታደሳለን" የሚለው የሰሞኑ ፈሊጣችሁ እንደ ስላቅም እንደ ጭንቀትም ሆኖ የሚታየው። በኣስርና መቶ ሺዎች ገድላችሁ፣ ኣሰራችሁ፣ ኣደህይታችሁ፣ ለስደት ዳርጋችሁ፥ ከዚሁ ከለመዳችሁት እኩይ ኣሰራር ላትላቀቁ፣ ሺ ጊዜ ተሃድሶ ብትሉ ኣይሰራም፥ የበሰበሰ ኣዕምሮ ቁምነገር ኣይወጣውምና የለውጥ ሂደት ባታደናቅፉ ይሻላል። ስዩም መስፍን በተሃድሶ " ከገባንበት ኣዘቅት በፍጥነት መውጣት ኣለብን - ኣለዚያ ኣወዳደቃችን ኣያምርም " ቢልም ለ25 ዓመታት የበሰበሰ ኣዕምሮ ኣሁን ይታደሳል ብሎ ማሰብ ከእባብ እንቁላል እርግብ መጠበቅ ሊሆን ነው። ይልቅስ ኣወዳደቃችሁ ብታሳምሩ ይሻላል እላለሁ። ይህን ስል ለናንተ ራርቼና በማይቀረው ውድቀታችሁ ኣዝኜ እንዳይመስላችሁ፣ ስትፈራገጡ በየቀኑ የምታጠፉት የሰው ህይወት፥ ከል የሚለብሱት ቤተሰቦች እና የሚወድመው የሃገር ሃብት ኣሳስቦኝ እንጂ።

ሰሞኑን በህዝቡ ማዕል ተደናግጣችሁ፥ ከተኛችሁበት የምኞት ወንበር ተቀስቅሳችሁ በሬድዮና ቲቪ የለቀቃችሁት የሰዓታት ልፈፋ በጣም ኣሰልቺና ኣሳፋሪ ነበር። ከዛ በላይ ደግሞ መሬት ላይ ካሉት እውነታዎች ምንኛ እንደተራራቃችሁና ያለቀላችሁ መደባዊ ቱጃሮች መሆናችሁን ኮለል ኣድርጎ የሚያሳይ ነው። ወደ ዝርዝሩ መግባት ጊዜ ማባከን ስለሚሆን፥ ያዋጣናል ብላችሁ ደጋግማችሁ በምታነስዋቸው 2 ነጥቦች ላይ ብቻ ምላሽ ልስጥ፣

1ኛ/ "ሕገ መንግስቱ የኢትዮጵያ ህዝቦች መብት ያስከበረ ነው"።

2ኛ/ "እድገታችን የፈጠረው ችግር" ለወቅቱ ህዝባዊ ተቃውሞ መንስኤ ሆነዋል፣ የሚሉ ናቸው።

በመጀመርያ ደረጃ ሕገ መንግስት ማለት የኣንድን ሃገር መሰረታዊ ሕጎችና ኣቁዋሞች ያጠቃለለ፣ የህዝቡ ኣመኔታ የተጎናጸፈ፣ በተለይ ደግሞ የመንግስታዊ ኣካላት ስልጣንን የሚገድብ የበላይ ሕግ ነው። እናንተ ግን እንደ ድርጅትም እንደ ግለ-ባለስልጣንም የሚያግዳችህ ሕግ ስለሌለ ሕገ መንግስት ኣለ ብሎ መናገር ኣይቻልም። ሕገ መንግስት እያላችሁ የምትመጻደቁበት ራሳችሁ ኣርቅቃችሁ የጨናችሁብን ቻርተር፣ ቀየት ብሎ ሕገ መንግስት የሚል ስም ተለጥፎበት በደጋፊዎቻችሁ የጸደቀ **ድርጅታዊ ፕሮግራም** ነው። ከኣቀራረጹም ከይዘቱም የህወሓት/ኢህኣዴግ ፕሮግራም እንጂ  ሕገ መንግስት ለመሆን ኣይበቃም። የኢትዮጵያ ህዝብም እንደ ሕገ መንግስቱ ኣያውቀውም። ስለዚህ ህዝቡ በነጻነት ላላጸደቀውና እውቅና ላልሰጠው ቻርተር ወይም 'ሕገ መንግስት' ተገዢ መሆን ኣይችልም። ኣይጠበቅበትምም። ስለ ሕገ መንግስት ኣቀራረጽና ተኣማኒነቱ ፕሮፌሰር ተስፋጽዮን መድሃኔ የደረሱት ጥናታዊ ጽሑፍ[i] ብታነቡ ፕሮግራማችሁን ኣጣጥፋችሁ በተቀመጣችሁ ነበር። ያም ሆኖ እናንተ እራሳችሁ ሕገ መንግስት ብላችሁ ያረቀቃችሁትን **ፕሮግራም** እየጣሳችሁ ያሻችሁን ስታደርጉ፣ ህዝቡ እንዲያከብርላችሁ መጠበቃችሁ የለየለት ኣምባገነንነት ኣልያም ጅልነት መሆኑን ብታውቁት ደግ ነው። ለመሆኑ ከሰነዱ ኣንቀጽ 10 ቁ. 1/2 ምን እንደሚል ታውቃላችሁ?

1. *ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፡ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው።*
2. *የዜጎች እና የህዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ።*

   *ይላል።*

ይበል እንጂ ስልጣን ላይ ከወጣችሁ ቀን ጀምሮ በተግባር ያየነው የዚሁ ግልባጭ የሆነው የመብት ረገጣና ኣጃቢው ኣራዊታዊ ጭካኔ ብቻ ነው። ስለዚህም  ሕገ መንግስት ኣስመልክቶ ኣንድ ቃልም ባይወጣችሁ ይመረጣል፣ ኣጉል መመጻደቅ ትርፉ ትዝብት ነውና።

ሁለተኛው ምክንያታችሁ “ዕድገታችን የፈጠረው ችግር” ለወቅቱ ህዝባዊ ተቃውሞ መንሳኤ ሆነዋል የሚለው ደግሞ ጨቅላዊ(infantile) ሰነ-ሞገት ነው። ዕድገት በመላ ዓለም እንደሚታወቀው  ስራ ሲፈጥር፣ ብልጽግና ሲያመጣ፣ ድርቅና ችጋር ሲያጠፋ ነው። ከ25 ዓመታት ኣገዛዛችሁ በሁዋላ በሃገራችን ሰፍኖ የሚታየው ደግሞ ስራ ኣጥነት፣ ድህነት፣ ድርቅና ችጋር ነው። የተባበሩት መንግስታት ዕድገት ፕሮግራም የኣምናው ሪፖርቱ (UNDP 2015 report HDI) እንደሚያሳየው 188 ሃገሮችን በ4 ክፍሎች (ሀ/ እጅግ ከፍትኛ፣ ለ/ ከፍትኛ፣ ሐ/ መካከለኛ፣ መ/ ዝቅተኛ) ብሎ ሲመድብ ኢትዮጵያን በዝቅተኛው ከማስቀመጡ ባሻገር  ወደ 174ኛ እርከን ዝቅ ኣድርገዋታል። በዚህ ላይ ድርቅን ተከትሎ የመጣው ችጋር ሰው-ሰራሽ ጥፋት መሆኑ ዓለም በተገነዘበበት በ21ኛው ክፍለ-ዘመን እናንት የምታቀርቡት ዘገባ ጭራሽ ኣሳፋሪ ከመሆኑ በላይ ከሳይንሳዊ ጥናት ርቃችሁ እንደተኛችሁ ያመላክታል። 25 ዓመታት ስልጣን ላይ ተቀምጣችሁ፥ በኣሁኑ ዓመት ብቻ 10.2 ሚሊዮን ህዝብ በረሃብ እስኪሰቃይ ጠብቃችሁ ምጽዋት ልመና በየበሩ ስታንኩዋኩ ብዙ ሰው ታዘበ፣ እንደለመዳችሁት በረሃብተኛው ስም የሚመጣው ዕርዳታ ከፊሉ ህዝባዊ ተቃውሞን ለማፈን ፥ ከፊሉ ደግሞ ኣልጠግብ ባይ ኪሳችሁን ለማወፈር መሆኑ ከምትሰሩት ፎቅና ቪላ፥ ከምታስነዱት ደብዛዛ መስተዋቱ መኪና፥ በየባንኩ ከምታጭቁት ገንዘብ ኣልፎ ለስለላ ብቻ ከምታወጡት ወጪ ማወቁ ከባድ እንዳይመስላችሁ። በኣንጻሩ ገባሩ ህዝቡ ኣፈር ገፍቶ፥ ኣፈር መስሎ በምግብ ለስራ ተመጽዋች ሆኖ ኣሁንም በሰቅጣጭ ኑሮ መማቀቁ ልትደብቁት ኣትችሉም። “ገጠርን ማእከል ያደረገ ልማት” የምትሉትን ማዘናጊያ ፈሊጥ ውጤቱ ችጋር መሆኑ ለ25 በተከታታይ መገንዘብ ተችለዋል። ያለፉት 16 ዓመታት የተባበሩት መንግስታት የዓለም ምግብ ፕሮግራም (WFP) እና የምግብና እርሻ ድርጅት (FAO) ሪፖርቶች መሰረት ያደረገ ጥናታዊ ጥንቅር እንደሚከተለው ያብራራል።

| Year (ዓመት) | Starving Ple. Millions (ረሓብተኛ በሚልዮን) | Source (ምንጭ) |
|---|---|---|
| 2000 | 2.3 | WFP |
| 2002-2003 | 12.6 | WFP |
| 2004 | 7 | FAO/WFP |
| 2006 | 7.2 | FAO |
| 2008 | 10 | FAO/WFP |
| 2009-2010 | 5 | FAO/WFP |
| 2011-2012 | 13 | WFP |
| 2013-2014 | +5 | WFP |
| 2015 | 10 | WFP |
| 2016 | 10.2 | FAO/WFP |

Table 1 — Mass starvation index 2000-2016 — Source: FAO and WFP (ቅንብር የኔ)

ታድያ በዓለም ከፍተኛ ከሚባሉት የ 11.5% ዕድገት ልፈፋችሁ ምንጩና ውጤቱ የት ላይ ነው? ምጽዋት ተግበስብሶ ኣዲስ የቱጃሮች መደብ ስለፈጠረ ዕድገት ሊሆን ኣይችልም። ዕድገት ባመዛኙ ችግር ቀራፊ

እንጂ ችግር ፈጣሪ ኣይደለም። ዕድገት ባለመኖሩ ነው ችግር የተፈጠረውና ችጋር የሰፈነው። ስለዚህም ችግር የፈጠረው "ዕድገታችሁ" ሳይሆን የማይረባ ፖሊሲያችሁ፣ ኣፋኝ ኣስተዳደራችሁ፣ የስልጣን ስስታችሁ፣ ቅጥ ያጣ ሙስናችሁ ተደማምሮ ነው። በነዚህ 2 ምክንያቶች ብቻ ስልጣን መልቀቅ ነበረባችሁ።

የህዝባዊው እምቢተኝነትና ተቃውሞ መነሻው ይኸው የናንተው የግፍ ኣገዛዝ ሆኖ እያለ፥ ኣንዴ በውጭ ሃይሎች፣ ሌላ ጊዜ በትምክህትና ጠባብነት ሃይሎች በማላከክ፣ ይባስ ብሎም የህዝቦች መተላለቅ እንዲከተል ትቀሰቅሳላችሁ። ኣባይ 'የርዋንዳ እልቂት'፥ ስዩም 'የኣይሁዶች ጭፍጨፋ-ሆሎከስትን' በማውሳት ህዝቡ ቢያንስ በፍርሓት እንዲሸማቀቅ እየጣራችሁ ነው። ግን ህዝቡ ኣርቆ ስለሚያስብ እኩይ ጥረታችሁ ሊሳካ ኣልቻለም። ኣልቀበታልና።

እንደሚታወቀው ማንም የውጭ ሃይል ለጥቅሙ ሲል ክፍተት ኣግኝቶ ይሁንና፥ ክፍተት ፈጥሮም እጅ ማስገባቱ እንዳለ ሆኖ፥ ታዲያ ክፍተት ፈጥሮ የውጭውን ጣልቃገብ የሳበ ኣካል በዋናነት ተጠያቂ መሆን ሲገባው ችግሩን በሌላ ማሳበብ ምን ይባላል? ይህ ክስተት የሞራልም የእውቀትም ደካማነት ያስከተለው ውስልትና ከመሆን ኣያልፍም።

ትምክህትና ጠባብነት ደግሞ ድሮም የነበሩ ኣሁንም ያሉ ወደፊትም በድፍረት እስካልተዋጋናቸው ድረስ ሊኖሩ የሚችሉ የሕብረተሰብ ነቀርሳዎች ናቸው። በነዚህ ነቀርሳዎች የተነሳ ደህና የነበረው ሰውም እንዲለከፍና እንዲከፋፈል ቦዩን የቀየሳችሁ እናንተው፣ ሕጋዊ ልባስ ኣግኝተው ያንሰራሩትም በናንተው ዘመን ነው። ከዚህ የተነሳ የሰከነ ውይይትና ጥናታዊ ዘገባ ተዳክሞ፥ ስነ-ሞገት ደብዝዞ፥ ኣጉል ንትርክና ቀረርቶ ጠፎ፥ **ጽንፈኝነት** እንዲስፋፋ ኣደረጋችሁ። በዚህ የጽንፈኝነት ወላፈን መከረኛው የትግራይ ህዝብ የጥቃቱ ዒላማ እንዲሆን ኣደረጋችሁ። የትግራይ ህዝብ ሰላምና ዕድገት ለኣያሌ ዘመናት ናፍቆ ኖሮ ህወሓት የመራውን ትግል ቢደግፍም ህልሙ እውን ሊሆን ኣልቻለም ብቻ ሳይሆን የባሰውን መከራ እንደወረደበት ኣርቆ ኣሳቢ የሆነ ሰው ሁሉ ሊረዳው የሚችል ሓቅ ነው። ስለዚህም በህወሓት ኣገዛዝ በችግርና በኣፈና የተወጠረ ህዝብ ህወሓትን የሚጠላበት እንጂ የሚደግፍበት ኣንድም ምክንያት የለውም። ከዴሞክራሲያዊና ሰብኣዊ መብቶቹ መገፈፍ ጀምሮ እስከ በድህነት ወጥመድ ተሸብቦ መኖር ያካተተ መከራ እየተጋተ ነው። እናንት በምቾት ጠምብሳችሁ፣ **ጽንፈኞቹ** ደግሞ በጥላቻ ተሸብበው የህዝቡን ኣሳዛኝ ሁኔታ መገንዘብ ኣልቻላችሁም።

የኣብዛኛዎቹ **ጽንፈኞች** ችግር የታሪክ ድንቁርና፥ የጥላቻ ፖለቲካና የማገናዘብ እጥረት ወዘተ ያስከተለው ጣጣ ሲሆን በተለይ በህዝብና በኣምባገነን መንግስት መካከል ያለው ሰፊ ልዩነት በቅጡ ያለመረዳት ተቀዳሚው እጥረት / ጎዶሎነት ነው። እናንት "የትግራይ ህዝብና ህወሓት ኣንድ ኣካል ነው" እንደምትሉት ሁሉ **ጽንፈኞችም** ይህነኑ እንዳለ ይሉታል። ኣንዳንድ የሚዲያ ተቀዋሚትም በሚያሳዝን ሁኔታ ይህንኑ ሲያራግቡ ይደመጣሉ። የ**ጽንፈኞቹ** ፍላጎት ህዝቡንም ደርቦ ለመምታት ሲሆን የናንተው ደግሞ በህዝቡ ጉያ ተወሽቆ ለመከላከል ነው። ሌላ ሚስጥር የለውም። የጥቂቶቹ ችግር ደግሞ ስግብግብነት ነው። ያው የናንተው ቅድ/ዓይነት መሆናቸው ነው። **ጽንፈኞቹ** ስልጣን ኣልያዙም እንጂ፥ ከቀናቸው እንደናንተው ስልጣኑና ሃብቱ ማግበስበስ ተቀዳሚ ሞያቸው እንደሚያደርጉ የሌሎች ሃገራት **ጽንፈኞች** እኩይ ታሪክ ያስገነዝበናል። የገብረመድህን ኣርኣያና የተክሌ ይሻው "በሬ ወለደ" ትረካ፥ ለዚሁ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። 'ጅብ በቀደደው ውሻ ይገባል' ተብሏል ኣይደል። የነዚህ **ጽንፈኞች** ሓላፊነት የጎደለው ትረካ - በዓለም-ኣቀፍ ሕግ ኣስጠያቂ የሆነው ኣደገኛ መዘዙ ሳንረሳ - ለጊዜው ኣቆይተን በኣንድ ልሂቅ ከተደረሰ ያልጠበቅኩት ጽሑፍ ላስነብባችሁ፦

‘ ህወሓት ሲመሰረት ያዘጋጀው የመርህ ሰነድ የአማራን ብሄር ዋና ጠላት ማድረጉ የአደባባይ ምስጢር ነው። እንዲህ ይላል። “ የአማራ ሕዝብ የትግራይ ህዝብ ዋና ወይንም አውራ ጠላት ነው። ይኼ ብቻ አይደለም የአማራ ሕዝብ የትግራይ ሕዝብ ድርብ ጠላት ነው። ስለሆነም፤ እኛ ( ህወሓቶች ) የአማራውን ሕዝብ መምታት አለብን፤ መጨረስ አለብን። አማራው ካልወደመ፤ አማራው ካልተደበደበ፤ ከመሬት ካልተነቀለ፤ የትግራይ ሕዝብ በነጻነት ሊኖር አይችልም። እኛ የምንመሰርተው ተተኪ መንግሥት ጥንቃቄ ማድረግ ያለበት አማራው ዋና መሰናክል እንደሚሆንብን ነው”።’ (ሰረዝ የኔ)።

**እንደዚህ የሚል ሰነድ ኣልነበረም ፣ የለምም።** ቀጥሎ በተሰራጨው ጽሑፋቸው ደግሞ ፦

‘ህወሓቶች፤ በተለይ የህወሓት መስራቾች፤ “ዐማራውን አህያ” ከማለት ደረጃ የደረሱበት የራሳችን ድክመት፤ ዝምታ ማብዛትና በጥቃቅን ነገሮች ለመተባበር አለመቻል ጭምር ነው።’ ይላሉ።

**ይህም ስድብ በህወሓት መስራቾች ኣልተባለም። ኣይባልምም።**

ሁለቱ የፈጠራ ጥቅሶች ‘በህወሓቶች’ ያተኮሩ ቢመስሉም፥ 1ኛ/ ከእውነት የራቁ ናቸው፥ 2ኛ/ ህዝብ ከህዝብ ጋር የማጋጨት እንደምታ ኣላቸው። የኣማራ ገዢ መደብ እንደጠላት መቁጠር ግን እውነት የመርህ ሰነድ ሆኖ ይገኛል። ይህ ማለት ደግሞ የሁለቱም ጭቁን ህዝቦች የመደብ ኣጋርነት ድሮም የነበር፥ ኣሁንም ያለ፥ ወደፊትም የሚኖር፥ ከታሪካዊነቱ ኣልፎም መሰረታዊ የህዝቦች መደባዊ ኣሰላለፍን የሚያመለክት የመርህ ሰነድ መሆኑ ነው። በውነት! ህወሓትን የምንቃወምበት ተራራ የሚያክሉ ዓበይት ሃገራዊ ወንጀሎች የሌሉ ይመስል፥ በማስረጃ የማይደገፉ ኣልፎም ህዝብን የሚያቃቅሩ ክሶች ላይ መንጠልጠል ለምን ኣስፈለገ ? ? ? የገብረመድህን ኣርኣያና የተክሌ ይሻው የጥላቻ ዘገባ እንደ ምንጭ የሚታሰብ ከሆነ ተያይዞ ገደል ውስጥ መግባት ነው። ይህ ዓይነቱ የዘውግ ፖለቲካ ዞሮ-ዞሮ ጉዳት እንጂ እርባና ስለሌለው ለጽንፈኞቹ ብቻ ቢተው፥ ዴሞክራቶችም በግልጽ ቢዋጉት ለሁላችን ይበጃል እላለሁ።

ሌላ ኣሳዛኝ ብሎም ኣደገኛ መልእክት ደግሞ ከኢሳት በኩል በጋዜጠኛ መሳይ መኮንን ተደምጠዋል። በከፊል እንዲህ ይላል፥ “እኛን የገጠመን ትግል በማንኛውም ዓለም እንደሚከሰተው በጨቋኝ መንግስትና በተጨቋኝ ህዝብ ተብሎ በሚጠራው መካከል ሳይሆን በኣንድ ዘራችሁን በማጥፋት የበላይ ሆኜ ልግዛ በሚል ጎሳና ፍዳው ኣላልቅ ባለው ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ነው። . . . ይህ የጥፋት እቅድ የታቀደው ከ5 ሚልዮን ህዝብ ለ95 ሚልዮን ህዝብ ነው። . . . ወደድንም ጠላንም ምርጫው . . . የተበላሸን ዓሳ ከባህር ማስወገጃ መንገዱ ኣንድ ነው፥ የባህር ውሃ ማስወገድ” [ii] እያለ ይቀጥላል። መረን የለቀቀ ዘረኝነት ይሉታል ይህ ነው። በኣምባገነኖቹና ጌቶቻቸው ሴራ የታፈነው ታጋይ ኣንዳርጋቸው ጽጌ ‘ነጻነት የማያውቅ ነጻ ኣውጪ’ በሚለው ሃያሲ መጽሓፉ “. . . ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች እንደሚሉት ወያኔ የያዘውን ስልጣን በመጠቀም ትግራይን ለመጥቀም በማሰብ ኣይደለም” (ገጽ.243)፣ “የወያኔ የጎሳ ፖለቲካ ፖሊሲ ከማንም ህዝብ፣ የትግራይን ህዝብም ጨምሮ፣ ደህንነት እና ጥቅም ጋር በቀጭን ክር እንኳን የተገናኘ ኣይደለም” (ገጽ 244)፥ ሲል መሳይ የገባው ኣይመስልም። በዛ ላይ! ኤርትራ ድረስ በመዝለቅ የጎበኛቸው በሺዎች የሚቆጠሩ የዴምህት (የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) ታጋዮች ከዚህ ግብታዊ ፍርድ ይተርፉ ይሆን? ይህ የዘር ማጥፋት ኣዋጅ በጋዜጠኛ መሳይ ተነበበ እንጂ ተደረሰ ለማለት ኣልደፍርም፣ ካንዴም ሁለቴ በቃለ-ምልልስ ጎን ተወያይተናልና። ያምሆኖ ግን የህወሓት/ኢህኣዴግ ጭፍጨፋዎች እንዳስመዘገብነው ሁሉ ይህን ዘግናኝ ጸረ-ህዝብ ኣዋጅም ወደሚመለከተው ዓለም-ኣቀፍ ተቋም ማስተላለፋችን ይታወቅልን። የመደብ ኣሰላለፍ ስነሓሳብን ያውቃሉ የሚባሉ ኣባላት ያሉበት ኢሳት ወደዚህ መውረዱ ኣሳዛኝም ኣስኮናኝም ነው።

‘ብሄሬ በኢትዮጵያዊነት እሳት ቀልጧል’ ያልው፥ ከጥላቻ ፖለቲካ የጸዳ፥ የምር ኢትዮጵያዊው የፍትሕ ታጋይ ተክለሚካኤል ኣበበ “የኛ ነገር፤ ትግሬን መነጠል፤ ሐሳዊ-ኢትዮጵያዊነት ነው”[iii] በሚል

ርእሰ ሰሞኑን የደረሰውን ኣርቆ-ኣመላካች ጽሑፍ ውስጥ **"የአማራ ህዝብ በስሙ ግፍ ከተሰራ፤ ግፍ ሰሪዎቹ እንጂ አማራው እንደማይጠየቀው ሁሉ፤ የትግራይ ህዝብም እንደዚያ በስሙ ለሚሰራ ግፍ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም . . . ትግሬን ብቻ ነጥሎ የሚከስ አካሄድ፤ ጸረ-ኢትዮጵያዊ ነው "** ይላል። እነዚህ ዓይነቶቹ ገንቢ ስነ-ጽሑፎች ብናነባቸውስ! (ሊገኩ ታች ኣለ)፣ ወይም ደግሞ ያለ ኣንድ ምክንያት 4 ዓመታት ከ 8 ወራት በግፍ ታስረው የተሰቃዩት የኢትዮጵያ ሙስሉሞች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ኣባላት መስከረም 1/2009 ዓ/ም ያካፈሉንን በሳል መልእክት ብናጤነውስ፣ ከገንቢ መግለጫቸው በከፊል፦

> *"ከየትኛውም ወገን የሚሰነዘሩ፣ ህዝብን ከህዝብ ሊያጋጩ የሚችሉ፣ አንዱን የተለየ ብሄር ወይም ማህበረሰብ አጠቃላይ በሆነ መልኩ የሚያወግዙ፣ የሚያስገልሉና በእኩይነት የሚፈርጁ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳዎች አገርን አደጋ ላይ የሚጥሉ በመሆናቸው ይህን መሰል ሁኔታ እንዳይፈጠር ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። የተለያዩ ባለድርሻ አካላትም ጸረ-ህዝብ እና አፍራሽ አካሄዶች እንዳይፈጠሩ የመከላከል ሰራቸውን ከመሰራት እንዲይዘናጉ አጥብቀን እናሳስባለን" ይላል።*

የህዝቦች ኣጋርነት ማጎልበት፥ የጽንፈኞች ሴራ ማክሸፍ፥ በጥቅሉ ኣርቆ-ኣሳቢነት ይሉታል በእንዲህ ያለ መርህ መቆም ነው።

የሁለት ስለት ሰለባ የሆነው የትግራይ ህዝብ ምን ዓይነት ኣጣብቂኝ ውስጥ እንደሚገኝ ማገናዘቡና ኢትዮጵያዊ ኣጋርነቱን እንደጥንቱ እንዲያጎለብት መተባበሩ ለምናካሂደው ስትራቴጃዊ የጋራ ትግል እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ የፍትሕ ወገን የሆነ ሁሉ የ"ድምጻችን ይሰማ" መርህ በኣጽናኦት ማስተጋባቱ ኣስፈላጊ ነው እላለሁ። እነዚህ ዓይነቱ ኣመለካከቶች የኢትዮጵያ መጪው ብሩህ ጊዜ መንገድ ቀያሾች ስለሆኑ በትጋት ልናስተጋባቸውም ይገባል።

እግረ-መንገዴ ያነሳሁት ኣሳሳቢ ጉዳይ እዚህ ላይ ልገድበውና ወደናንተ ወደ ቱጃሮቹ ልመለስ። የዛ ሁሉ የጥላቻ ፖለቲካ ሰበብ እናንተው የወቅቱ ባለስልጣኖቹ፥ ሕጋዊ ሽፋን በመስጠት ያራመዳችሁት የዘውግ ፖለቲካ መሆኑ ደጋግሜ ላሰምርበት እፈልጋለሁ፣ በኣጽናኦት።

ኣሁን በሃገራችን ላንሰራራው ኣጠቃላይ ዝቅጠት ዋናው ተጠያቂ፣ ራሳችሁ በትክክል እንደገመገማችሁት የናንተው "የበሰበሰ ኣመራር" ሆኖ እያለ በናንተ ኣሰራር ምክንያት ሁሌም ገፈት ቀማሹ፣ መከራ ተሸካሚውና ኣፈናው ኣላላውስ ያለው የትግራይ ህዝብ ኣብሮ ተወቃሽ የሚያደርጉ ድምጾች መሰማታቸው የባሰውኑ ልብን የሚያቆስል ነው። የደርግ ኣመራርን ከሰራዊቱና ከህዝቡ ጋር ደምሮ መምታት እንደማለትም ነው። ስር የሰደደው የናንተው (የህወሓት/ኢህኣዴግ) ክፉ ኣገዛዝ እንዳይበቃው፣ ኣፋኙና ታፋኙ፥ ድሃውና ቱጃሩ፥ ገዢውና ተገዢው የማይለይ ውርጅብኝ በህዝቡ ላይ ማወረድ ለምንስ ኣስፈለገ? ከላይ በናንተው ጩካኝ ኣፈና፣ ከታች ደግሞ ህዝቡን ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ የሚነጥል ጉንተላ፣ ውስጥ ተወጥሮ ያለው ህዝብ ኣንድነቱን ኣሳምሮ ሲነሳ ቀን ግን ግብኣተ-መሬታችሁ መሆኑ እወቁት። ይህ ደግሞ ሩቅ ኣይደለም።

በርግጥ ኣይቀሬ ውድቀታችሁ ከጀመረ ውሎ ኣድሮዋል። እየተቀላጠፈም ነው። ምናልባት ከሙስና ጨካ ውስጥ መሽጋችሁ የከበብዋችሁን ተራሮች ላይታይዋችሁ፥ የተቀጣጠለው የእምቢተኝነት ድምጽ ላይሰማችሁ ይችላል። ቀደም ሲል "ድምጻችን ይሰማ" በሚል መርህ የተነሳው የሙስሊም ወገናችን እንቅስቃሴ፣ ቀጥሎ በኦሮሞው፥ በኣማራው፥ በሲዳማው፥ በጋምቤላው፥ በኣፋሩ፥ በኦጋዴኑ . . . .ወዘተ ትግሉ ተፋፍመዋል። በትግራይም እንዲሁ ለጊዜው ያዳፈናችሁት የተምቤን ዓቢይ-ዓዲ፥ የኣጽቢ፥ የነበለት፥ የመቀሌው ፍትሕ ፍለጋ እምቢተኝነት ተጠናክሮ ዳግም ይነሳ ዘንድ እየተፋፋመ ነው። ሰዩም **"ከገባንበት ኣዘቅት በፍጥነት መውጣት ኣለብን፣ . . . ኣለዚያ ኣወዳደቃችን ኣያምርም"** ስትል ስለ ኣወዳደቁ ዓይነት (ማማር ወይም ኣለማማር) ብቻ ሳይሆን ውድቀቱም የጀመረ ለመሆኑ የገባህ ይመስላል። እንግዲህ የኣወዳደቁ

ምርጫ ለናንተ የሚተው ሆኖ፣ ያሉትን ኣማራጩ ከሚታገልዋችሁ የፖለቲካ ሃይሎች ኣንጻር ልጠቁም ፣ ከትግራይ ብጀምር 1. ዓረና ትግራይ በሰላማዊ ምርጫ፥ 2. ዴምህት በትጥቅ ትግል፥ 3. ትዴት/ታንድ በህዝባዊ ኣመጽ፥ የሚሉ ሆነው እነዚህ ሶስት ኣማራጮች በሃገር ደረጃም ተጠቃለው የሚቀርቡ ናቸው፣ ማለትም ዓረና በመድረክ፥ ዴምህት በኣርበኞች ግ/7፥ ትዴት በሸንጎ ተደራጅተው ይቀርባሉ። ከፖለቲካ ሃይሎች ውጭ ደግሞ ኣያሌ ግለሰቦችና የሲቪክ ንቅናቄዎች የየበኩላቸው ኣማራጮች እያቀረቡ ይገኛሉ። በስደት ከሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ሽዎችን የሚወክሉ 34ቱ "ውረዱና የሽግግር መንግስት ይቋቋምበት" የሚል የማያወላዳ መፍትሄ ሰንዝረዋል።

ተጠቃሎ ሲታይ ኣማራጮቹ ከጥገናዊ ለውጥ ጀምሮ እስከ ስር-ነቀል ለውጥ ያካተቱ ቢሆንም ዞሮዞሮ የናንተው ኣምባገነናዊ ስርዓት ተወግዶ በህዝባዊ-ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መተካት እንዳለበት መደምደሚያው ነው። ስለሆነም የኣወዳደቅ ዓይነቱ ምርጫ ለናንት ለቱጃሮቹ እየተውኩ፥ የሁኔታው ኣጣዳፊነት ግን ተጨባጭ መሆኑ ከሰማችሁኝ ላስገነዝባችህ እወዳለሁ። ዘመኑ ደንቆሮም የሚሰማበት ጊዜ ነውና! (በምልክትቋንቋ/sign language):: በእውነት ጊዜው ደርሰዋል፣ ያንድ ትውልድ ዘመን ስልጣን ላይ ተቀምጣችሁ፥ ሰለሞን ነጋሽ "የትግራይ ህዝብና የህወሓት ግኑኝነት ነባራዊ ገጽታ"[iv] በሚል ርእስ በጥልቀት እንደተነተነው 80% የትግራይ ህዝብን የምግብ ለስራ/ሴፊቲ-ኔት ተመጽዋች በማድረግ ለመናጢ ድህነት ዳርጋችሁ፣ መላው የኢትዮጵያ ህዝብም በዚሁ ሁኔታ እንዲኖር እያስገደዳችሁ፥ እናንት የናጠጡ ቱጃሮች ሆናችሁ ስልጣን ላይ እንቆያለን ማለት ከዕብደት ያልራቀ ቅዠት ነው።

ኣፈናም ሆነ ሙስና፥ ክልል-ዘር-ሃይማኖት የለውምና ጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ የ25 ዓመታት የኣፈናና የግድያ የድህነት ኣገዛዝ በቃኝ! በቃኝ! በቃኝ! "ፍርሓት ኣለቀብኝ" ብሎ ከጫፍጫፍ ተነስቶባችሁ ይገኛል። የመላ ኢትዮጵያዊ ግንዛቤ የሚወክል በወንድም ሠማነህ ርቱዕ ኣንደበት ከተላከልን ሰፊ ሓተታ ቀንጭቤ ላካፍላችሁ፣ "በስልጣን ላይ ያሉት ሰዎች አሁን የሚታያቸው የሃገራቸው፣ የኢትዮጵያዊያን፤ የትግራይ ክፍለሃገርና የትግራይ ሕዝብ ሁኔታ ሳይሆን ንብረታቸው፤ ጥቅማቸውና ስልጣናቸው ብቻ ነው። . . . " ይላል። ደረቅ ሓቅ ኣይደል! ስልጣን ላይ ደግሞ ለዘለዓለም ኣይኖርም። ሃገሮች የ4፥ የ5 ወይም የ8 ዓመታት የስልጣን ገደብ የሚደነግጉት ያለምክንያት እንዳልሆነ ይግባችሁ። ሰሞኑን በጎንደር ኣሁን ደግሞ በብሸፍቱ ወገኖቻችን ላይ ያካሄዳችሁት ኣሰቃቂ ጭፍጨፋ ኣራዊታዊ ባህሪያችሁ የሚያጋልጥ ተጨማሪ የውድቀታችሁ ምልክት ነውና ይብቃችሁ። እንደ ህዝቡ እናንተም በቃን በሉ። ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ፍቱ። ከያቅጣጫው የሚዘንበው የመፍትሄ ጥሪ ኣዳምጡና ተግብሩ። ኣለዚያ ብርሌው ነቅቷልና መንኮታኮት የግድ ይላል።

የትግራይ ህዝብ በኣምባገነኖች ኣይገዛም!!!

የህዝቦች ኣንድነት ይለምልም!!!

የትግራይ ኢትዮጵያዊነት በመሰሪዎች ኣይናድም!!!

ኢትዮጵያ በሩቅ-ኣሳቢ ልጆችዋ ህብረት ትነሳለች!!!

---

**ተጠቃሾች** ፦ (ሁሉንም በምልኣት ማጤን ይበጃል !)

[i] ተስፋጽዮን መድሃኔ (ፕ/ር) ፣ “Constitution-making, Legitimacy and Regional Integration: An Approach to Eritrea’s Predicament and Relations with Ethiopia” http://vbn.aau.dk/files/16138517/diiper_wp_9.pdf

[ii] መሳይ መኮንን https://www.youtube.com/watch?v=GvQ6jC5t7KE

[iii] ተክለሚካኤል አበበ ፣ “የኛ ነገር፤ ትግሬን መነጠል፤ ሐሳዊ-ኢትዮጵያዊነት ነው” ፣ www.ethiomedia.com/1016notes/isolating_tigrians.pdf

[iv] ሰለሞን ነጋሽ ፣ “የትግራይ ህዝብና የህወሓት ግኑኝነት ነባራዊ ገጽታ” ፣ ZeHabesha.com፣ http://www.zehabesha.com/amharic/archives/66682